የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ ቁጥር 791/2013

ሐምሌ 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# <u>የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ</u>

በቴሌኮም ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ የቴሌኮም ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የሚመራበት እና የሚተዳደርበት አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ማበጀት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች የተቀናጀ የቴሌኮሚኒክሽን አገልግሎትን በመላው ሃገሪቱ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ እና ከፍተኛ ጥራት ባለው መልኩ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመታመኑ፤

ተጠቃሚዎች አገልግሎት ከሚሰጣቸው አገልግሎት ሰጪ አካል ውጪ በሃገሪቱ ውስጥ ከሚገኝ አገልግሎት ሰጪዎች ተጨማሪ አገልግሎት የሚያገኙበት ስርዓትን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

በኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(2) ፥6 (13) ፥43 (1) እና 54(2) መሰረት ባለስልጣኑ ይህንን የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ ቁጥር 791/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) **"ባለሥልጣን"** ማለት በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤
2) **"ኢንተርኮኔክሽን"** ማለት በተለያዩ የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል አካላዊ፥ ቴክኒካዊ እና ምክንያታዊ የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትዎርክ ግንኙነት መፍጠር ሲሆን በዚህም የአንድ የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ከሌላ የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተሮች ተጠቃሚዎች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ ማስቻል ወይም በሌላ የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡
3) **"አገናኝ ኦፕሬተሮች"** ማለት እርስ በእርስ ኔትዎርካቸውን የሚያገናኙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ናቸው፤
4) **" ኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ"** ማለት ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶችን የሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ነው፤
5) **" የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች"** ማለት የእርስ በእርስ የኔትዎርክ ትስስር ለመፍጠር በማሰብ አንድ የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተር ለሌላ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጠው አገልግሎት ነው፡፡ አባሪ አንድ የእነዚህን አገልግሎቶች ዝርዝር እና ማብራሪያዎች ይዟል፤

6) **"የኢንተርኮኔክሽን ቦታ"** ማለት ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች በጋራ ስምምነት ኔትወርኮቻቸውን የሚያገናኙበት በቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ውስጥ ያለ ቦታ ነው፤

7) **" የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ"** ማለት ለኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የተዘጋጀ መደበኛ ቅፅ ነው፤

8) **" የኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ ኦፕሬተር"** ማለት ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ኢንተርኮኔክሽን የሚጠየቅ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ነው፤

9) **" የቴሌኮሙኒኬሽን የችርቻሮ አገልግሎት"** ለተጠቃሚ በቀጥታ የሚቀርብ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሲሆን ለቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የሚቀርብ አገልግሎትን አይጨምርም።

10) **'የስራ ቀናት'** ማለት ስራ የሚሰራባቸው ቀናቶችን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ቅዳሜ፥ እሁድ፥ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ባሕላት ተብለው የተለዩ ቀናቶችን አይጨምርም።

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ቀዳሚ ዓላማ፤

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች የሚተዳደሩበት ማዕቀፍ ማበጀት ነው።

2) በአዋጁ አንቀጽ 42 እና አንቀጽ 43 መሠረት ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶችን ለመቆጣጠር ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ደንቦች እና ሥነ ሥርዓቶች ግልጽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።

3) የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ የተቀናጁ እና ወጥነት ያላቸው የቴሌኮሙኒክሽን አገልግሎቶች እንዲሰጡ ማስቻል ነው።

4) እያንዳንዱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ተጠቃሚ ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ተጠቃሚ ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ማስቻል ነው።

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚገኙ በሁሉም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት
# የባለሥልጣኑ ሚና

## 5. የባለሥልጣኑ ሚና

1) ባለሥልጣኑ

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባቶችን ይፈታል፤ እንዲሁም በዚህ መመሪያ በተመለከተው የግዜ ገደብ ውስጥ በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል በቂ የኔትወርክ ትስስር እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፤

(ለ) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚፈጠረውን ኢንተርኮኔክሽን የሚያስተዳድሩ ህጎች በከፍተኛ ደረጃ ተአማኒነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ በማዘጋጀት በባለሥልጣኑ እንዲያጸድቁ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ እና

(ሐ) የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ጸድቀው ተግባራዊ ከሆኑ ማናቸውም መመሪያዎች ጋር የተጣጠመ መሆኑን ገምግሞ ያጸድቃል፡፡

2) በአዋጁ አንቀጽ 43 መሠረት ባለሥልጣኑ፤

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ጸድቀው ተግባራዊ ከሆኑ ማናቸውም መመሪያዎች ጋር የተጣጠመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይገመግማል፡፡

(ለ) በራሱ ተነሳሽነት ወይም የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ሲጠይቅ ጣልቃ በመግባት በአዋጁ፤ በዚህ መመሪያ ወይም በባለስልጣኑ ጸድቆ ተግባራዊ ከሆነ ማንኛውም መመሪያ ጋር የማይጣጣሙ የኢንተርኮኔሽን ስምምነት ድንጋጌዎችን ይለውጣል ወይም አስገዳጅ ውሳኔዎችን ይሰጣል፡፡

(ሐ) ተዋዋይ ወገኖች በኢንተርኮኔክሽን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት ኔትወርካቸውን ማገናኘት ካልቻሉ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት ጣልቃ ሊገባ ይችላል፤ ተገቢ ሆኖ ከተገኘም የኢንተርኮኔክሽን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን ይወስናል፤ እና

(መ) በራሱ ተነሳሽነት ወይም በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገን ጠያቂነት ጣልቃ በመግባት በዚህ መመሪያ በተደነገገው ያለመግባባት መፍቻ ሥርዓት መሠረት የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባቶችን ይፈታል፡፡

## ክፍል ሦስት
## አጠቃላይ የኢንተርኮኔክሽን መርሆዎች

### 6. ግልጽነት

1) ባለሥልጣኑ በኢንተርኮኔክሽን ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ሂደቶች የሚታዩ እና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ በባለሥልጣኑ የፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ እንዲታተም እና ለኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ በነጻ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ያፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ በድረ ገፁ ላይ ያወጣል፤

### 7. አድልዎ አለማድረግ

አድልዎ ያለማድረግ መርህ የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት አቅራቢ አሁናዊ እና ወደፊት የሚመጡ አገልግሎቶችን የተመለከቱ የኢንተርኮኔክሽን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች፥ የአገልግሎት የቴክኒክ ደረጃዎችን፣ አስተማማኝነትን፣ ጥራትን እና ክፍያን ጨምሮ የኔትዎርክ ቴክኖሎጂዎች ለራሱ ወይም ለሌላ ኦፐሬተር ከሚያቀርብበት ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡

### 8. ሕጋዊ ክፍያዎች

የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶት አቅራቢዎች የሚያስከፍሉት ክፍያዎች ትክክለኛ፣ ምክንያታዊ፥ ወጪን መሰረት ያደረገ እና በኢንተርኮኔክሽን ጠያቂዎች መካከል ተገቢ ያልሆነ ልዩነት የሚፈጥር መሆን የለበትም፡፡

9. <u>የአገናኝ ኦፕሬተር መብቶች እና ግዴታዎች</u>

1) አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ጥቅም ላይ ያዋለው ደጋፊ ቴክኖሎጂ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች የመጠየቅ መብት እና ሲጠየቅ ስለኢንተርኮኔክሽን የመደራደር እና በቴክኒክ ደረጃ አዋጪ በሆኑ አካባቢዎች ኔትዎርኩን የማገኛኘት ግዴታ አለበት፡፡

2) አገናኝ ኦፕሬተሮች የእያንዳንዳቸውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ኔትወርክ ለማቀድ፣ ለመገንባት፣ ለመዘርጋት ወይም ለመጠበቅ አንዱ ከሌላው ተገቢነት ያላቸውን መረጃዎች የመጠየቅ እና የመቀበል መብት አላቸው፡፡

3) አገናኝ ኦፕሬተሮች በዚህ መመሪያ መሠረት የተቀበሉትን መረጃ ለተጠየቀበት ዓላማ ብቻ መጠቀም እና የመረጃውን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረቶች ማድረግ አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>የኢንተርኮኔክሽን ሥነ ሥርዓቶች</u>

10. <u>በቅን ልቦና የሚደረግ ድርድር</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች ላይ የሚደረግ ድርድር በተሳታፊ የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል በቅን ልቦና መካሄድ አለበት፡፡ እንዲሁም አገናኝ ኦፕሬተሮች ከኢንተርኮኔክሽን ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችን ለመፍታት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

2) በቅን ልቦና በሚደረጉ ድርድሮች ላይ እያንዳንዱ ተደራዳሪ ወገን የሚከተሉትን ማድረግ የለበትም፤

(ሀ) ሆን ብሎ ሌላኛውን ወገን ማሳሳት ፤

(ለ) ሌላውን ተዋዋይ ወገን በማስገደድ የማይፈልገውን ስምምነት ላይ እንዲደርስ ማድረግ፤ እና ፣

(ሐ) ሆን ብሎ ድርድርን ማደናቀፍ፤

3) በቅን ልቦና የመደራደር መርሆዎችን መጣስ የሚከተሉትን ያካትታል፤

(ሀ) ለሌላው ኦፕሬተር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ሁሉ በወቅቱ አለመስጠትን፤

(ለ) ጫና የሚያሳድሩ ወይም ያለአግባብ የተለጠጡ ወይም ገደብ የሚጥሉ ሚስጥርን ያለመግለጽ ስምምነቶች እንዲፈረሙ ማስገደድን፤

(ሐ) ለወደፊት ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚፈቅድ ድንጋጌ በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ውስጥ እንዲካተት አለመፍቀድን፤

(መ) በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች ከጉዳዩ ጋር የማይዛመዱ ጉዳዮችን እልባት ከመስጠት ጋር ለማያያዝ መሞከርን፤

(ሠ) ወጪን መሰረት ያላደረጉ ክፍያዎችን መጠየቅ፤

(ረ) ምክንያታዊ ያልሆኑ ድንጋጌዎችን እና ሁኔታዎችን ማቅረብ፤

(ሰ) ድርድርን የሚያዘገዩ ድርጊቶችን መፈጸም፥ አስገዳጅ ሁኔታዎች ውስጥ ለመግባት ሥልጣን ያለውን ሰው ለመሰየም በተደጋጋሚ ፈቃደኛ አለመሆንን ጨምሮ እና ሌሎች ሁኔታዎች፤ እና

(ሸ) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በቅን ልቦና የሚደረግ ድርድር መርህን የሚጥሱ ሁኔታዎች ናቸው ብሎ የሚወስናቸውን ሌሎች ጉዳዮችን፤

## 11. የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ

1) አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሌላ ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄውን እንደሚከተለው ማቅረብ ይኖርበታል፤

(ሀ) ለተጠያቂው ኦፕሬተር በጽሑፍ ማቅረብ ፣

(ለ) የሚፈለገው የኢንተርኮኔክሽን ዓይነት፣ ድርድሩን ለመጀመር የታሰበበትን ቀን፣ ኢንተርኮኔክሽኑ የሚፈለግበትን ቀን፣ የሚያስፈልገው የኢንተርኮኔክሽን አቅም ግምትን ጨምሮ ሌሎች መረጃዎች ማካተት፤ እና

(ሐ) ጥያቄውን ለኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ባቀረብ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍማሳወቅ።

2) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄን በተቀበለ በአስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ

(ሀ) ከኢንተርኮኔክሽን ጋር የተያያዙ ደርድሮችን በታቀደው ቀን መጀመር፤

(ለ) የተጠየቀውን የኢንተርኮኔክሽን ዓይነት ማቅረብ፤ እና

(ሐ) በኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ ኦፕሬተር በቀረበው የጊዜ ወሰን ውስጥ ኢንተርኮኔክሽኑን ማከናወን፤

መቻል አለመቻሉን ለጠያቂው ኦፕሬተር በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል

3) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር የተጠየቀውን ኢንተርኮኔክሽን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን ለኢንተርኮኔክሽን ጠያቂው ኦፕሬተር ከገለጸ፦

ሀ) የጸደቀውን የኢንተርኮኔክሽኑን አቅርቦት መነሻ ሰነድ ኮፒን መስጠት እና

ለ) የኢንተርኮኔክሽኑ ጥያቄ በቀረበ ከአስር (10) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ድርድሩን መጀመር፤ ይኖርበታል።

4) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር እና የኢንተርኮኔክሽን ጠያቂው ኦፕሬተር በቅን ልቦና መደራደርና ድርድሩን ለማጠናቀቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ጥረት በማድረግ ድርድሩ በተጀመረ ከአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መፈራረም ይኖርባቸዋል።

5) የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ ውድቅ የሚደረገው የቀረበው ጥያቄ ከቴክኒክ አንጻር የማያስኬድ ወይም ከፋይናንስ አንፃር አዋጪ ካልሆነ እና የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር ጥያቄውን በተቀበለ ከአስር (10) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጥያቄው ወድቅ ከተደረገበት ምክንያት ጋር በጽሑፍ ሲገልጽ ነው። ከፋይናንስ አንጻር አዋጭ አይደለም የሚባለው የሚታይ የፋይናንስ ጉዳት ያስከትላል ተብሎ በባለስልጣኑ ሲወሰን ነው።

6) የኢንተርኮኔክሽ ጥያቄው ከቴክኒክ አንጻር ለመመዘን ከታች የተመለከቱ መስፈርቶችን ጨምሮ ሌሎችንም ያካትታል፦

ሀ) ጥያቄው በቀረበበት ወቅት የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢን የኔትዎርክ የቴክኒክ መሰፈርት ያሟላ መሆን አለበት እና

ለ) ለኢንተርኮኔክሽን ጠያቂው አገልግሎቱን መስጠት በኢንተርኮኔክሽን አቅራቢው ኔትዎርክ፥ የኔትዎርክ መሰረታዊ ፥ አቅም ወይም አስተማማኝነት ላይ አሉታዊ ተጽህኖ የማያደርስ ከሆነ ነው።

7) የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄን ለማስተናገድ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢውን ኔትዎርክ ማሻሻል የሚያስፈልግ ከሆነ ከማሻሻያው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ምክንያታዊ ወጪን የኢንተርኮኔክሽን ጠያቂው ይሸፍናል።

8) የኢንተርኮኔክሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽኑን ጥያቄ ውድቅ የተደረገበትን ቅጂ ውድቅ የተደረገበት ውሳኔ ለጠያቂው ኦፕሬተር በደረሰው ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል ውስጥ እንዲያያዝ ማድረግ ይኖርበታል።

9) በአዋጁ አንቀጽ 43(2) መሠረት ኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽኑን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ወይም ተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ኢንተርኮኔክሽኑ ስምምነት ካልተጠናቀቀ ከተዋዋዮቹ ወገኖች አንዱ ለባለሥልጣኑ ይግባኝ ማቅረብ ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ በመግባት በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ አንቀጽ 38 ወይም ባለሥልጣኑ ሙግትን ለመፍታት ባወጣው መመሪያ መሠረት አስገዳጅ ውሳኔ መስጠት ይችላል።

## ክፍል አምስት
## የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች

### 12. የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች

1) በቴሌኮመኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረጉ ሁሉም የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች በጽሑፍ ሆነው፤

(ሀ) በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት የተመለከቱ መርሆዎችን የተከተሉ፣

(ለ) በኢንተርኮኔክሽን ተዋዋይ ወገኖች ፈቃዶች ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን የሚያከብሩ ፣

(ሐ) በኢንዱስትሪው በስፋት ተቀባይነት ያገኙ ወይም በባለሥልጣኑ የፀደቁ ደረጃዎችን የሚያሟሉ፤ እና

(መ) ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ከወጣ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ጋር የተጣጣሙ፤

መሆን ይኖርባቸዋል።

2) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት አገናኝ ኦፕሬተሮች በህግ መሠረት ማቅረብ የሚችሉትን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገድብ ወይም እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሆን የለበትም።

3) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢን ወይም የኢንተርኮኔክሽን ፈላጊን ከሌላ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ወይም የኢንተርኮኔክሽን ፈላጊ ጋር ተጨማሪ ስምምነት እንዳያደርግ የሚከለክል መሆን የለበትም።

## 13. <u>የኢንተርኮኔክሽን ስምምነትን ፋይል ስለማድረግ</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ከተፈረመ በኋላ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር የስምምነቱን ቅጂ ስምምነቱ በተፈረመ ከአስር (10) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከባለሥልጣኑ ፋይል ጋር እንዲያያዝ ማድረግ አለበት።

2) ባለሥልጣኑ የስምምነቱን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን መገምገም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከአገናኝ ኦፕሬተሮች ተጨማሪ መረጃዎች መጠየቅ ይችላል።

## 14. <u>የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች ስለማሻሻል</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በጋራ ስምምነት ስምምነቱን ማሻሻል ወይም ማስተካከል ይችላሉ። የተሻሻለው ወይም የተስተካከለው ስምምነት ማሻሻያው በተደረገ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከባለሥልጣኑ ፋይል ጋር መያያዝ አለበት።

2) በአዋጁ አንቀጽ 43(2) መሠረት ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በአንዱ የቀረበን ጥያቄ በመከተል የኢንተርኮኔክሽኑን ስምምነትን ማሻሻል የሚችለው ስምምነቱ ወይም ድንጋጌው፤

(ሀ) ከአዋጁ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ሲሆን፤

(ለ) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ሲሆን፤

(ሐ) በባለሥልጣኑ ከጸደቀና ተፈጻሚነት ካለው ማንኛውም የመመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሲሆን፤ ወይም

(መ) የሕዝብን ጥቅም የማያስጠብቅ ሲሆን፤

ነው።

3) ባለሥልጣኑ ጣልቃ በመግባት የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ለማስተካከል ሲወስን ማሻሻያው ግልጽ በሆነ መንገድ በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሥነ ሥርዓቶች በመከተል መወሰን አለበት፤

(ሀ) በሥራ ላይ ያለውን የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ለማሻሻል የቁጥጥር ሂደቱ መጀመሩን በጉዳይ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች በሕዝብ ማስታወቂያ ያሳውቃል። ማስታወቂያውም የትኛው የስምምነቱ ድንጋጌ፦

(1) ከአዋጁ ድንጋጌ ጋር እንደሚቃረን፤

(2) ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር እንደሚቃረን፤

(3) በባለሥልጣኑ ካፀደቀውና ተፈጻሚነት ካለው ማንኛውም መመሪያ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር እንደሚቃረን፤ ወይም

(4) የሕዝብን ጥቅም እንደማያስጠብቅ፤

የሚያሳይ ግልጽ መግለጫ የያዘ መሆን ይኖርበታል።

(ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱት መግለጫዎች የታሰበውን ማሻሻያ እና ለማሻሻያው የተሰጠውን አሳማኝ ምክንያት ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡

(ሐ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች ለስምምነቱ በማሻሻያነት በቀረበው ሃሣብ ላይ ምላሽ ወይም አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

(መ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየቶችን ከተቀበለ በኂላ በሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ውስጥ የተቀበላቸውን አስተያየቶች በተመለከተ፤

(1) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ወይም

(2) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ከሆነ በስምምነቱ ላይ የተጠቆሙ ለውጦችን ያደርጋል፤ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ዙር በተቀመጠው ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ይፈቅዳል፡፡

(ሠ) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

(ረ) ባለሥልጣኑ በተቀበለው አስተያየት ላይ የሰጠውን ምላሽ እና የመጨረሻውን ውሳኔ በድረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

(ሰ) ጉዳዩ በሚታይበት ወቅት በጉዳዩ ያገባኛል በሚሉ ወገኖች ለባለሥልጣኑ የተሰጡ መረጃዎች ሚስጥራዊነትን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌዎች የባለሥልጣኑን የመቆጣጠር እና የመከታተል ሥልጣን ተግባራዊ ከማድረግ የሚያደናቅፍ መሆን የለበትም፡፡

## 15. <u>የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት መቋረጥ</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የሚቋረጠው በስምምነቱ የተመለከቱትን የውል ቃሎች በጥብቅ በመከተል መሆን አለበት፡፡

2) ባለስልጣኑ ዘንድ የተያያዘን የኢንተርኮኔክሽን ስምምነትን ማቋረጥ የፈለገ ተዋዋይ ወገን የውሉን ማቋረጫ ምክንያቶች በመጥቀስ ለሌላው ወገን ከስልሣ (60) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ በመሥጠት በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

3) የተፈጸመ ጥሰት በሚኖርበት ወቅት ማስጠንቀቂያ ሰጪው ኦፕሬተር ለሌላው ተዋዋይ ወገን ጥሰቱን እንዲያስተካክል ከሠላሣ (30) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ወገን ጥሰቱን ካላስተካከለ ማስታወቂያ የሰጠው ወገን ተጨማሪ ሰላሳ (30) የስራ ቀናት የውል ማቋረጫ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱን ያቋርጣል ወይም በባለሥልጣኑ ሙጉት መፍቻ መመሪያ መሠረት ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ ይችላል፡፡

4) የኢንተርኮኔክሽኑ ስምምነት ሊቋረጥበት እንደሆነ ማስጠንቀቂያ የተላከለት ተዋዋይ ወገን በባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በዚህ ግዜ ባለስልጣኑ የሙጉት መፍቻ መመሪያን መሠረት በማድረግ ጣልቃ ይገባል፡፡

5) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነትን በራሱ ወይም ከኢንተርኮኒክሽን ጠያቂ ጋር በመስማማት ያቋረጠ ከሆነ ፤ ስምምነቱ በተቋረጠ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና የስምምነት ማቋራጫ ማስታወቂያ ኮፒ ለባልሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## 16. <u>የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ</u>

1) የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ ለኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የተዘጋጀ መደበኛ ቅፅ ሲሆን በተለያዩ ክፍል የተከፈሉ አግባብነት ያላቸው የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች እና ክፍያን ጨምሮ ተያያዥ ህግን እና ሁኔታዎች አካቶ የያዘ ነው፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ በአንቀጽ 7 ላይ የተመለከተ የኢንተርኮኔክሽን መርህን ያካተተ እና በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆን አለበት፡፡

3) ሁሉም የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነዳቸውን ባለስልጣኑ ፊት ቀርበው እንዲያጸድቁ ትዕዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ ባለስልጣኑ ጋር ፋይል መደረግ አለበት፡፡

4) ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የኢንተርኮኔክሽኑን ማጣቀሻ ሰነድ መገምገም እና ለህትመት ብቁ መሆን አለመሆኑን መወሰን ወይም በቀረበው ሰነድ የተካተቱትን ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን ጣልቃ በመግባት በሃያ (20) የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ማሻሻያ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን ጥያቄ በሃያ (20) የሥራ ቀናት ውስጥ ውድቅ ካላደረገው ወይም ጣልቃ በመግባት የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነዱን ካላሻሻለው የቀረበው ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

5) በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ የጸደቀ የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ ሌላ የተሻሻለ የኢንተርኮኔክሽን መነሻ ሰነድ እስከሚፀድቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡

6) የፀደቀ የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ ያለው ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ኦፕሬተር የተሻሻለ የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ እንዲፀድቅ በባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ሊያደርግ ይችላል፡፡

7) ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ በመገምገም ለህትመት እንዲበቃ የሚያፀድቀው መሆን አለመሆኑን በአስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን ጥያቄ በበአስር (10) የሥራ ቀናት ውድቅ ካላደረገው ወይም ጣልቃ ገብቶ ሰነዱን ካላሻሻለው የተሻሻለው የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

8) ባለሥልጣኑ በእርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች፤

   (ሀ) የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ ወይም የሰነዱ ማናቸውም ድንጋጌ ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ ወይም በባለሥልጣኑ ከፀደቀና ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ፤ ወይም

   (ለ) ባለሥልጣኑ ጣልቃ መግባቱ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሀኖ ካገኘው ፡፡

   በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የቀረበን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጣልቃ በመግባት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

9) ባለሥልጣኑ በእርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ ጣልቃ በመግባት ለማሻሻል ከወሰነ በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና

ከዚህ በታች የተመለከቱትን በመከተል ተገቢ የሆኑትን ማሻሻያዎች ግልጽ በሆነ አሠራር መወሰን አለበት፤

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነዱን ለማሻሻል የቁጥጥር ሂደት መጀመሩን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት በጉዳዩ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች ያሳውቃል፡፡ ማስታወቂያውም የትኛው ድንጋጌ እንደሚሻሻልና ለምን እንደሚሻሻል የሚያሳይ ግልጽ የሆነ መግለጫ የያዘ ሆኖ ሰነዱ፤

(1) በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤

(2) ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ ወይም

(3) በባለሥልጣኑ በፀደቀ ተፈጻሚነት ካለው ማንኛውም መመሪያ ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን ወይም

(4) የሕዝብን ጥቅም የማያስጠብቅ መሆኑን፤

ማሳየት ይኖርበታል፡፡

(ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9)(ሀ) የተመለከተው መግለጫ በማሻሻያነት የቀረበውን ሃሣብ እና የማሻሻያውን አሳማኝ ምክንያቶች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

(ሐ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በማሻሻያ ሃሣቡ ላይ ምላሽ እና አስተያየት እንዲሰጡ ከአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

(መ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየት ከተቀበለ በኋላ በተቀበለው አስተያየት ላይ ምላሹን በአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በምላሹም፤

(1) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ወይም

(2) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ከሆነ በቀረበው ሃሣብ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ዙር በተቀመጠው ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

(ሠ) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

(ረ) በቀጥጥሩ ሂደት ባለሥልጣኑ በተቀበለው አስተያየት ላይ የሰጠውን ምላሽ እና የመጨረሻውን ውሳኔ በድረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

ሰ) በቁጥጥሩ ሂደት ወቅት በጉዳዩ ያገባኛል በሚሉ ወገኖች ለባለሥልጣኑ የተሰጡ መረጃዎች በሚስጥርነት መጠበቅ እስካለባቸው ድረስ ባለሥልጣኑ የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

10) የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ የሚቀርበውን የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች ዝርዝር ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን፣ የቴክኒክ ደረጃዎች እንዲሁም በኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች አቅራቢ የሚተገበሩ የደህንነት ደረጃዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

11) የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ የአገልግሎት ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች እንዴት እንደሚሻሻሉ የሚገልጽ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት።

12) የኢንተርኮኔክሽን ማጣቀሻ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

(ሀ) የስምምነት ማዕቀፍ ፤

(ለ) የሚሰጠው የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች መግለጫ፤

(ሐ) ለቁሳዊ ኮሎኬሽን ዓላማ ሁሉም የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች እና የተደራሽነት ሁኔታዎች መግለጫ፤

(መ) ውጤታማ የሆነ ኢንተርኮኔክሽንን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ የቴክኒክ መስፈርቶች፤

(ሠ) ለኢንተርኮኔክሽን ኔትዎርክ የሚያገለግሉ የማሠራጫ ቴክኖሎጂዎች የቴክኒክ ዝርዝሮች፣ የቴክኒክ ደረጃዎች ወይም ፕሮቶኮሎች፤

(ረ) የመጀመሪያ ኢንተርኮኔክሽን አተገባበር እና የአሠራር ሂደቶት ሥነ-ሥርዓት ፣ ተግባራዊ ሙከራዎች፤ ቀጣይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ፤ ዕቅድን፣ የኔትወርክ ትራፊክን እና የክፍተት አስተዳደር እና የጥገና ሥርዐቶችን፤

(ሰ) የአንድ ጊዜ ክፍያዎችን፣ ተደጋጋሚ ክፍያዎችን፣ ክፍያዎችን፣ የክፍያ ሥርዐቶችን እና የውል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን ጨምሮ ንግድ ነክ ጉዳዮች፤

(ሸ) የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶችን ማቅረቢያ የጊዜ ገደብን ፣ የአገልግሎት ጥራት መስፈርቶችን እና ግዴታን ባለማክበር የሚጣሉ መቀጮዎችን ያካተተ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ስምምነት።

## ክፍል ስድስት
## የኢንተርኮኔክሽን ክፍያዎች

### 17. የኢንተርኮኔክሽን ክፍያዎች

1) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ከኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ ይልቅ ከእርሱ ጋር የቅርብ ትስስር ላለው ደርጅት የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ ዋጋ ወይም ሁኔታዎች መስጠት አይችልም።

2) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎትን ምክንያታዊ በሆነ ዋጋ ማቅረብ ያለበት ሲሆን በሌላ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ለእሱ ከሚሰጠው የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት ዋጋ ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም።

3) ለኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ፤

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 በተመለከቱት መርሆዎች መሠረት፤

(ለ) የኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ ኦፕሬተር ለተጠየቁት አገልግሎቶች የግድ አስፈላጊ ላልሆኑ የኔትወርክ ዘርፎች ወይም ዝግጅቶች ክፍያ እንዳይፈጽም እያንዳንዱን አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ተነጣጥለው እንዲደራጁ የሚያደርግ፤ እና

(ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 43 መሰረት በተዋዋይ አካላት መካከል የተደረገ ድርድር እና ስምምነት።

መሆን ይኖርበታል።

4) የኢንተርኮኔክሽን ክፍያዎች ተለይተው፤

(ሀ) ለቁሳዊ ኢንተርኮኔክሽን ማቋቋሚያ እና ማስፈጸሚያ ቋሚ የአንድ ጊዜ ክፍያዎች፤

(ለ) ጥቅም ላይ እየዋለ ላለ መሣሪያ፣ የኔትወርክ ክፍል ወይም መገልገያዎች በየጊዜው የሚከፈሉ ክፍያዎች፤

(ሐ) በአቅም ወይም በአጠቃቀም ላይ የተመሠረቱ የትራፊክ ማስተላለፊያ ክፍያዎች፤ እና

(መ) ለተጨማሪ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ተለዋዋጭ ክፍያዎች፤

ራሳቸውን ችለው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

5) የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት መስጫ ክፍያዎችን የሚከተሉት መንገዶች በመጠቀም የሚሰላ ይሆናሉ፦

ሀ) በረዥም ግዜ ሊወጣ የሚችል ተገማች የሆነ ወጪ፤

ለ) ተመጣጣኝ የሆነ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አሁናዊ ወጪ፤

ሐ) በውድድር ገበያ ውስጥ የሚፈጠሩ የወጪ መጠን፤እና

መ) ውጤታማ ውድድርን የሚያበረታታ ጤናማ እና አግባብነት ያለው የወጪ መጠን፤

6) የዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 3(ሐ) እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 43 መሰረት የኢንተርኮኔክሽን ክፍያን ይወስናል፡፡

## 18. የሂሳብ መዝገብ መለያየት

1) ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን በችርቻሮ የሚሸጥ ከሆነ ፣ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢው የአገልግሎቶቹ አካል የሆኑትን ወጪዎችና ገቢዎች ሁሉ ለመለየት የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶቹን በሕግ መሠረት ራሱን ችሎ እንደሚያከናውን ኩባንያ በተለዩ የሂሣብ መዝገቦች መያዝ ይኖርበታል፡፡

2) ባለሥልጣኑ የችርቻሮ አገልግሎቶች በሚሰጡ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢዎች የሂሳብ መዝገብ መለያየት እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን የሚደነግጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## የኢንተርኮኔክሽን የቴክኒክ ጉዳዮች

## 19. የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች

1) የኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ የሥርዓት ሁኔታዎች እና ሌሎች መስፈርቶችን ለመገምገም እንዲያስችለው ትስስሩን ማድረግ ስለሚፈልግበት ቦታ ወይም ቦታዎች የተሟላ ዝርዝር ሊያሳውቀው ይገባል፡፡

2) አገናኝ ኦፕሬተሮች የራሳቸውን የኔትወርክ ትራፊክ ወደ ኢንተርኮኔክሽን ቦታ የማጓጓዣ ወጪን ጨምሮ ለግንባታ ወጭ እና የኔትወርክ ግንኙነትን ለመደገፍ ከተጓዳኝ መሣሪያዎች እና የማዞሪያ አቅም ጋር የራሳቸውን የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች የመጠገን ሃላፊነት አለባቸው፡፡

3) የኢንተርኮኔክሽን ቦታ መገኛዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

ሀ) የሞባይል ማዞሪያ ማዕከል;

ለ) የሚዲያ መግቢያ በሮች;

ሐ) የአካባቢያዊ ልውውጥ ማዞሪያ

መ) የታንደም ልውውጥ ማዞሪያ እና

ሠ) ሌላ ለንግድ ወይም ቴክኒካዊ ለሆኑ ነገሮች አመቺ የሆኑ ቦታዎች፡፡

4) የኢንተርኮኔክሽን ጠያቂው ኦፕሬተር ለኢንተርኮኔክሽን የሚውሉ መሳሪያዎቹ ከኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ መሳሪያዎች እና ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ እንዲቀመጥ ከጠየቀ አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ፣ የአገልግሎቱ ክፍያ በተዋዋይ ወገኖቹ በጋራ ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 20. የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች ጥራት

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት መለስተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን የሚያካትት፣ ዓለም ዓቀፍ የኢንዱስትሪ ልምዶችን ያገናዘበ እና የአገልግሎት ደረጃዎችን ለአለማሟላት ተገቢ መፍሔዎችን የሚያስቀምጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን ጥራት እና የአገልግሎት ደረጃ አድልዎ ካለማድረግ መርህ ጋር ተጣጥሞ መሄድ ያለበት ሲሆን በዚህም የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር የሚያቀርው የአገልግሎት ደረጃ ለራሱ ወይም ለሌላ ኦፕሬተር ከሚያቀርበው የጥራት እና የአገልግሎት ደረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡

3) የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድን ጨምሮ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች፤

(ሀ) የኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች፣ የትራፊክ መስመሮች እና በኔትወርክ መሣሪያዎች መካከል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ የመሳሰሉትን የአገልግሎት አቀራረብ እና የቴክኒክ ባህርያትን፤

(ለ) የአሠራርና የጥገና ሁኔታዎች እና ተዛማጅ የአፈጻጸም መለኪያዎችን፤

(ሐ) የአገልግሎት ጥራት አመላካቾች፤ እና

(መ) መፍቴሔዎች፥ ክፍያዎች እና የአገልግሎት አስጣጥ ደረጃ ስምምነትን ባለማክበር የሚጣሉ መቀጮዎች፤

የሚገልጽ ወይም የሚደነግግ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ስምምነት ማካተት አለበት፡፡

4) የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ስምምነት አሁናዊ እንዲሁም ወደፊት ለሚመጡ አገልግሎቶች ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የወደፊት ቴክኖሎጂ ለውጥን መሰረት በማድረግ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 21. የኢንተርኮኔክሽን የቴክኒክ መስፈርቶች

1) የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ወይም የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን ቴክኒካዊ መረጃዎች ማካተት አለበት፤

(ሀ) ቁሳዊ የኢንተርኮኔክሽን ዓይነት፤

(1) የቀረበውን ቁሳዊ የኢንተርኮኔክሽን ዓይነት ማለትም በኢንተርኮኔክሽን አቅራቢው ኦፕሬተር ወይም በኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ ኦፕሬተር ወይም በእያንዳንዱ ኦፕሬተር ጣቢያ መካከል የሚገኝ፤

(2) ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በኢንተርኮኔክሽን ቦታዎች ምርጫ ላይ ውጤታማ ምርጫ እንዲያደርጉ የሚያስችል ካርታን እና የኔትወርክ ንድፍን ጨምሮ ለኢንተርኮኔክሽን የቀረቡ የቦታዎች ዝርዝር፤

(3) ለእያንዳንዱ የኢንተርኮኔክሽን ቦታ አግባብነት ያላቸው የቴክኒክ መስፈርቶች እና ደረጃዎች በሙሉ፤

(4) ለኔትወርክ ዕቅድ አግባብነት ያላቸው የቴክኒክ መስፈርቶች እና ደረጃዎች በሙሉ፤

(5) በተጠያቂው ኦፐሬተር ኔትወርክ ውስጥ የኢንተርኮኔክሽን ቦታ ማቋቋም፣ ቦታ መቀየር ወይም ማንሳት ተግባራት የሚፈጸሙባቸው ሥርዓቶች፡፡

(ለ) የኢንተርኮኔክሽን ኔትወርክ ማዞሪያ

(1) ትራፊክን ለማገናኘት የሚያስፈልጉ የማዞሪያ አቅም መስፈርቶችን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ ደንቦች እና ሥርዓቶች፤

(2) የኢንተርኮኔክሽን ማዞሪያ የሚከናወንበት ቦታዎች (ዓለምዓቀፍ መግቢያ በር፣ የከተማ መገናኛ፣ የአገር ውስጥ ማዞሪያ ወዘተ.) ደረጃ መለየት ወይም አይፒ ኢንተርኮኔክሽንን በተመለከተ በየትኛው የትራንስፖርት ንብርብር ትስስሩ እንደሚከናወን፤

(ሐ) ማያያዝ እና ማስተላለፍ

የኢንተርኮኔክሽን ማያያዣ የሁለቱን ኦፕሬተሮች ኔትወርኮችን የሚያገናኝ ሲሆን የሚከተሉተን ማካተት አለበት

(ሀ) የማስተላለፊያ አቅም፤

(ለ) የማስተላላፊያው ስፋት፣ እና

ሐ) የማስተላለፊያው ብዛት፤

(መ) ሲግናል

ተገናኝ ኦፕሬተሮች በኢንዱስትሪው አጠቃላይ ተቀባይነት ካለው ዓለም ዓቀፍ ደረጃዎች ጋር በሚጣጣሙ የሲግናል ደረጃዎች ላይ መስማማት አለባቸው፡፡

(ሠ) ተጣጣፊነት

(1) ተገናኝ ኦፐሬሮች ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላ ጫፍ የሚያቀርቡት አገልግሎቶች

የኢንዱስትሪ የአስተማማኝነት ደረጃ የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፤

(2) የተጣጣፊነት አቅም ፍተሻ የሚከወንበት ደንቦች እና ሥርዓቶች የኔትወርክ አስተማማኝነትን እና የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎቶች መስተጋብርን ለማረጋገጥ የሚከወን ፍተሻ ነው፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ በኢንተርኮኔክሽኑ አገልግሎቶች ላይ ሊደረጉ ስለታሰቡ ወይም ስለታቀዱ ማናቸውንም ለውጦች ለሚገናኘው ኦፕሬተር በቂ የሆነ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት እና በለውጡ ምክንያት በኢንተርኮኔክሽኑ አገልግሎት ላይ ሊደርስ የሚችል ጎጂ ጉዳትን እንዲቀንስ ሊጠይቀው ይገባል፡፡

22. <u>ስለቁጥር አሰጣጥ</u>

አገናኝ ኦፕሬተሮች አንዱ ለሌላኛው በየራሳቸው ኔትወርኮች ስላሉት ቁጥሮች መረጃ መሰጣጣት አለባቸው፡፡ ይህም የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት አካል ሆኖ ስምምነቱ ይፈረምበታል ተብሎ ከሚታሰበው ቀን በፊት ቀደም ብሎ ነው፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>
## <u>ሕትመት</u>

23.. <u>በባለሥልጣኑ የሚታተም የኢንተርኮኔክሽን መረጃ</u>

1) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶችን እና የኢንተርኮኔክሽን አቅርቦት መነሻ ሰነድን ጨምሮ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆኑ የኢንተርኮኔክሽን ጉዳዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ያሳትማል ወይም መታተማቸውን ያረጋግጣል፡፡

2) የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ የአገልግሎት ታሪፎችን ባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለበት፡፡ ባሥልጣኑ መረጃዎቹን በራሱ ድረ ገጽ ሊያወጣው ይችላል፡፡

3) ሁሉም የቴሌኮመኒኬሽን ኦፕሬተሮች ከባለሥልጣኑ ምክንያታዊ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ኢንተርኮኔክሽንን የሚመለከቱ የተለዩ መረጃዎችን ሁሉ ለባለሥልጣኑ መስጠት አለባቸው፡፡ ባለሥልጣኑ የኢንተርኮኔክሽኑን ተዋዋይ ወገኖች የንግድ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅን ትኩረት በመስጠት የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>
## <u>አለመግባባትን ስለመፍታት</u>

24. <u>የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባትን ስለመፍታት</u>

1) በኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ኦፕሬተር እና ጠያቂ ኦፕሬተር መካከል የኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት የተጠየቀበት አግባብነት ወይም ለኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት ተገቢ ያልሆነ ክፍያ መጠየቅን በተመለከተ አለመግባባት ከተፈጠረ ወይም ተዋዋይ ወገኖች ኢንተርኮኔክሽንን በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም የገቡበትን ስምምነት ተግባራዊ ማድረግ ካልቻሉ፣ ከሁለቱ አካላት አንዱ ባለስልጣኑ አለመግባባቱ እንዲፈታ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2) አለመግበባቱን እንዲፈታ ለባለስልጣኑ ጥያቄ ያቀረበው አካል፣ ጥያቄውን በጽሁፍ በማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉበት ቀን ጀምሮ ከሠላሳ (30) የስራ ቀናት ባልበለጠ ግዜ ውስጥ ጥያቄውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ የቀረበውን የጽሁፍ ጥያቄ ተከትሎ ጥያቄውን በተቀበለ በአስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ፣

(ሀ) ጣልቃ ለመግባት ወይም ላለመግባት ከመወሰኑ በፊት ከተዋዋይ ወገኖቹ ተጨማሪ መረጃዎችን የመጠየቅ፣

(ለ) ጣልቃ ላለመግባት ከወሰነ ላለመግባት የወሰነበትን ከእነ አሳማኝ ምክንያቱ በጽሑፍ የማስፈር፣ ወይም

(ሐ) በባለሥልጣኑ የክርክር መፍቻ መመሪያ በተደነገጉት ሥርዓቶች መሠረት ጣልቃ ለመግባት መወሰኑን፤

ለጠያቂው ወገን ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

4) የኢንተርኮኔክሽን አለመግባባት በመፈታት ሂደት ላይ እያለ በማንኛውም ሁኔታ ከሁለቱ ወገኖች በአንዱ ኢንተርኮኔክሽኑ አይቋረጥም ።

## ክፍል አስር

## ሕግ ማስፈጸም እና ሕግ ማክበር

### 25. ሕግ ማክበር

ባለስልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ እና የኢንተርኮኔክሽን ተቀባይ የአዋጁን እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎችን ማክበራቸውን ይቆጣጠራል።

### 26. ሕግ ማስፈጸም

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ፥ አዋጁ እና ባለስልጣኑ ያጸደቃቸውን መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የኢንተርኮኔክሽን አቅራቢ ወይም የኢንተርኮኔክሽን ጠያቂ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ከወሰነ፤ በአዋጁ አንቀጽ 52 መሰረት እርምጃ የሚወስድ ሲሆን እርምጃው የገንዘብ ቅጣት ወይም ካሳ ሊሆን ይችላል።
2) የዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የሚወስደው እርምጃ እና ቅጣት የሚመራው በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መሰረት የሚንስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ሲሆን በዚህ ደንብ የትኞቹ መተላለፎች የፈቃድ መሰረዝ፥ መታገድ እና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደሚያስከትሉ የሚያመለክት ሲሆን ቅጣቶችን ለይቶ የሚያስቀምጥ እና የሚጣለው የመቀጮ ገንዘብ መጠን ይወስናል።

## ክፍል አስራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 27. ማሻሻያ

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር እንዲሁም ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል።

### 28. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 2 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 2 ቀን 2013 ዓ.ም**

**ኢንጂነር ባልቻ ሬባ**
**ዋና ዳይሬክተር**
**የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን**

# <u>አባሪ ሀ</u>

## <u>የኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን አገልግሎት አይነቶች ማብራሪያ</u>

የሚከተሉት የአገልግሎት ምድቦች ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው የተለመዱ የኔትወርክ ኢንተርኮኔክሽን አይነቶችን ለማሳየት የቀረቡ ናቸው፡፡

1) **የጅምላ የመደበኛ ጥሪ የማገናኘት አገልግሎት** ፡ የመደበኛ ድምጽ አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር (አያያዥ ኦፕሬተር) የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ይመለከታል፡፡ አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል፡፡ የአያያዥ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን ጥሪ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚመጡ ጥሪዎችን ጨምሮ በራሱ ኔትወርክ ላይ ጥሪዎችን በማስተላለፍ በተጠሪው ወገን ማለትም የአያያዥ ኔትወርክ ላይ ወደሚገኙ ደንበኞች ያገናኛል፡፡

2) **የሞባይል ጥሪ የጅምላ የማገናኘት አገልግሎት** ፡ የሞባይል ድምጽ አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር (አያያዥ ኦፕሬተር) የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ይመለከታል፡፡ አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል፡፡ የአያያዥ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን ጥሪ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚመጡ ጥሪዎችን ጨምሮ በራሱ ኔትወርክ ላይ ጥሪዎችን በማስተላለፍ በተጠሪው ወገን ማለትም የአያያዥ ኔትወርክ ላይ ወደሚገኙ ደንበኞች ያገናኛል፡፡

3) **የአጭር መልዕክት አገልግሎት የማገናኘት አገልግሎት**፡ በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የመልዕክት አገልግሎት ነው፡፡ አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል፡፡ የአገናኝ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን የአጭር መልዕክት አገልግሎት በራሱ ኔትወርክ ላይ የአጭር መልዕክት አገልግሎት በማስተላለፍ በተቀባዩ ወገን ማለትም የአያያዥ ኔትወርክ ላይ ከሚገኙ ደንበኞች ጋር ያገናኛል፡፡

4) **የመልቲሚዲያ መልዕክት አገልግሎት የማገናኘት አገልግሎት**፡ በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የመልዕክት አገልግሎት ነው፡፡ አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ ሌላ ኦፕሬተርንም ሊያካትት ይችላል፡፡ የአያያዥ ኦፕሬተር ኔትወርክ ከሌላ ኦፕሬተር ኔትወርክ የመጣውን የመልቲሚዲያ መልዕክት አገልግሎት በራሱ ኔትወርክ ላይ የመልቲሚዲያ መልዕክት አገልግሎት በማስተላለፍ በተቀባዩ ወገን ማለትም የአያያዥ ኔትወርክ ላይ ወደሚገኙ ደንበኞች ያገናኛል፡፡

5) **የጅምላ የትራንዚት ኢንተርኮኔክሽን**፡ ጥሪው ከመጣበት አካባቢ ኔትወርክ በሌለው እና አያያዥ ኦፕሬተር ባልሆነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ያመለክታል፡፡ አገልግሎቱ ለሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚገኝ ሌላ ኦፕሬተር የሚሰጥ ነው፡

6) **የመደበኛ ጥሪ መነሻ የጅምላ አገልግሎት**፡ የመደበኛ ድምጽ አገልግሎት ለደንበኞቹ በሚያቀርብ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር (አቅራቢ ኦፕሬተር) የሚሰጥ የጥሪ ማስተላለፍ አገልግሎትን ይመለከታል፡፡ አቅራቢ ኦፕሬተር በራሱ ኔትወርክ ላይ ያለን ጥሪ ለትራንዚት ጅምላ ሽያጭ ወይም የጥሪ ማስተላለፍ ጅምላ ሽያጭ ወደ የኢንተርኮኔክሽን ቦታ ያስተላልፋል፡፡ የመደበኛ ጥሪ ጅምላ ሽያጭ አቅርቦት አገልግሎት አስተላላፊ የመምረጥ አገልግሎት አቅርቦትን ለማመቻቸት ያስችላል፡፡ ይህ አገልግሎት ከቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ጋር የተገናኙ ደንበኞች ለመደበኛ የድምጽ ጥሪ ሌላ አገልግሎት አቅራቢን መምረጥ የሚችሉበትን ዕድል ይሰጣል፡፡

7) **የመስመር ኪራይ የጅምላ አገልግሎት፡** አስቀድሞ በተመሰረተ አቅም እና በአግባቡ በሚመራ የኔትዎርክ ማስተላላፍ አገልግሎት አማካኝነት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚደረግ የማስተላለፍ አገልግሎት ነው፡፡ ይህ አገልግሎት፡፡ይህ አገልግሎት በዋና የኔትዎርክ ማስተላለፊያ ወይም መደራሻ ሊሰጥ ይችላል፡፡
8) **የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ አገልግሎት፡** የጠያቂ ሞባይል ኦፐሬተር ደንበኛ በተጠያቂ የሞባይል ኦፕሬተር ኔትዎርክ ላይ እንዲስተናገድ ማድረግ ሲሆን በዚህም ደንበኛው የራሱ ኦፐሬተር የኔትዎርክ ተደራሽነት በሌለው አከባቢ ላይ አገልግሎት እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡
9) **የኢንተርኔት ትራንዚት አገልግሎት፡** የኢንተርኔት ትራንዚት አገልግሎት ወይም የአይፒ ትራንዚት አገልግሎት የጠያቂ ኦፕሬተር የኢንተርኔት ትራፊክ ከአለምአቀፍ የኢንተርኔት ትራፊክ ጋር መገናኘት እንዲችል በተጠያቂ ኦፐሬተር ለጠያቂ ኦፐሬተር የሚሰጥ አገልግሎትን ይመለከታል፡፡
10) **በቀጥታ ዳታ የመለዋወጥ አገልግሎት፡** ሁለት የተለያዩ እራሳቸውን የቻሉ የቴሌኮሙኒኬሽኖች ኦፕሬተሮች በመካከላቸው ያለውን የዳታ ትራፊክ በቀጥታ የሚለዋወጡበት እና ከዓለም አቀፍ ኢንተርኔት ጋር የሚገናኙበት አገልግሎት ነው፡፡ በቀጥታ ዳታ የመለዋወጠ አገልግሎት ከክፍያ ነጻ ወይም በክፍያ ሊሆን ይችላል፡፡